# የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ የዞን ጽዳት አጠባበቅ እና የስታንዳርድ አፈፃፀም የአሰራር መመሪያ ቁጥር 24/2013

Solid Waste Collection, Zonal Cleaning Maintenance and Standards Implementation Guidelines for Cooperative Cleaning Associations (Directive No. 24/2013)

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ

Addis Ababa City Administration
Solid Waste Management Agency

ሚያዚያ 1፥ 2011

# 1. መግቢያ

በከተማችን አዲስ አበባ ከሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 75 ፐርሰንት የሚሆነው ከመኖሪያ ቤት ይመነጫል፡፡ ይህ ከመኖሪያ ቤት የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በአካባቢና በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት ሳያደርስ በአግባቡ ሰብስቦ ለማጓጓዝ የከተማው አስተዳደር ከ6,000 በላይ ዜጎችን በጥቃቅንና አነስተኛ የጽዳት ማህበራት በማደራጀት ከቤት ለቤት የደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብ ስርዓት ከ15 ዓመት በፊት ከተማው ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

በተለይ በ2010 ዓ.ም የጥቃቅንና አነስተኛ የጽዳት ማህበራትን አቅም ለማሳደግና የደረቅ ቆሻሻ ከመኖሪያ ቤት አሰባሰብ ስርዓቱን በተሻለ ቴክኖሎጂ በማገዝ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ስርዓቱን ለማዘመን ሲባል በጥቃቅንና አነስተኛ የጽዳት ማህበራት የተደራጁትን ማህበራት በአቅራቢያቸው በሚመች ሁኔታ በማዋሃድ ወደ 74 የሽርክና ማህበራት እንዲያድጉ በማድረግ የተሻለ አሰራር እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

እነዚህን የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ለማስተዳደር የሚያስችልና ከተማዋ አሁን ካላት የእድገት ደረጃ ጋር ሊመጥን የሚችል የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የአሰራር መመሪያ የነበረ ሲሆን ካለው ሁኔታ በማቃኘት አሻሽሎ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፯/፪ሺ፲ አንቀጽ ፴፫ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን በተመለከተ ለኤጀንሲው በከተማው ካቢኔ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በማድረግ ይህንን የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ የዞን ጽዳት አጠባበቅና የስታንዳርድ አፈጻጸም የአሰራር መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የአሰራር መመሪያ ቁጥር ፳፩/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ዓላማ

- የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ለከተማው ነዋሪ ህብረትሰብ የሚሰጡትን የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ስርዓት ግልጽ፣ ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋ እና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን በማድረግ አሰራሩን በማዘመን ከተማዋን ጽዱና ውብ ማድረግ ነው፡፡

### ፫. የቃላት ትርጓሜ

የቃላት አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

፩. ***"ከተማ"*** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. ***"ኤጀንሲ"*** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

፫. ***"ደረቅ ቆሻሻ"*** ማለት የንብረቱ ባለቤት ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማይፈለግ ብሎ የሚጥለው ጠጣር ወይም ከፊል ጠጣር የሆነ ቁስ ነው፡፡

፬. ***"መሰብሰብ"*** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ከመኖሪያ ቤት የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ወደ ጊዚያዊ ማቆያ ማዕከል በአነስተኛ ተሽከርካሪ ማጓጓዝ ነው፡፡

፭. ***"የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር"*** ማለት ደረቅ ቆሻሻን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ መኖሪያ ቤቶችና ከዞን ጽዳት ለመሰብሰብ በሽርክና ወይም በዩኒዬን የተደራጁ የጽዳት ማህበራት ናቸው፡፡

፮. ***"15 ፐርሰንት ማበረታቻ"*** ማለት ደረቅ ቆሻሻ ከመኖሪያ ቤት ለመሰብሰብ በአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ጸድቆ ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከሚከፈለው ክፍያ ውስጥ 15 ፐርሰንቱ የዞን ጽዳትና ለነዋሪው ህብረተሰብ በሳምንት ሁለቴ (በስታንዳርድ) አገልግሎት መስጠቱ በሚመለከታቸው አካላት ተረጋግጦ ለማህበራቱ የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡

፯. ***"ዞን"*** ማለት የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ ደረቅ ቆሻሻ እንዲሰበስብበት በወረዳው ወይንም በክፍለ ከተማው ተከልሎ የተሰጠው የስራ ቦታ ነው፡፡

## ፬. መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከመኖሪያ ቤት የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ቤት ለቤት እየተሰበሰበ በጊዜያዊ ማከማቻ ቦታ እንዲከማች በማድረግ በመንግስት ተሸከርካሪ ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዲጓጓዝ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እነዚህ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ደረቅ ቆሻሻን ከቤት ለቤት የሚሰበስቡበት የአሰራር መመሪያ በ1997 ዓ.ም ተዘጋጅቶ እንደወቅቱ ሁኔታ እየተሻሻለ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ይህ መመሪያ አሁን ከተማዋ ካላት የእድገት ደረጃና ህብረተሰቡ የሚጠይቀውን የጽዳት አገልግሎት ጥያቄ ሊፈታ በሚችል መልኩ ያልተዘጋጀ ሲሆን በተጨማሪም በመመሪያው ላይ የተቀመጠው የቁጥጥርና የተጠያቂነት ስርዓቱ ውስንነት ያለበት በመሆኑ እንደገና አሻሽሎ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

ስለሆነም አሁን በከተማዋ የሚመነጨውን የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ሰብስቦ ለማጓጓዝ፤ የከተማው ህብረተሰብ በስታንዳርዱ መሰረት በሳምንት ሁለቴ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ለማድረግ፤ የአካባቢ ወይም የዞን ፅዳት በተሻለ እንዲጠበቅ እና ከመኖሪያ ቤት የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታትና ጠንካራ የቁጥጥርና የተጠያቂነት ስርዓት በመዘርጋት የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ስርዓቱን ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ይህ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ፭. የመመሪያው ወሰን

- የዚህ መመሪያ ወሰን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ በሚሰበስቡ በሁሉም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ፮. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ስርዓት

፩. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ የሚችለው ከመኖሪያ ቤት፤ በተለያዩ አካላት ከአካባቢ ጽዳት የተሰበሰበን ወይም ማህበሩ ከዞን ጽዳት በራሱ የሰበሰበውንና በዞኑ በህገ-ወጥ መንገድ የተጣሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ነው፡፡

፪. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ ከተለያዩ ድርጅቶችና የገበያ ማዕከላት ደረቅ ቆሻሻን መሰብሰብ አይችልም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር አገልግሎት በሚሰጥበት ዞን የሚገኙ የተለያዩ ተቋማትና ድርጅቶች በግል የጽዳት ድርጅት የደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብ አገልግሎት የማያገኙ ከሆነ ከወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር በዞኑ የሚገኙ ተቋማትና ድርጅቶች የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ በግል የጽዳት ድርጅት እንዲሰበሰብ እስከሚደረግ ድረስ ብቻ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር አገልግሎቱን እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

፬. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻን ከመኖሪያ ቤት የሚሰበስበው ቤት ለቤት በመሄድ ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፬ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንደሚኒዬም መኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻን ቤት ለቤት በየህንጻው ለመሰብሰብ አስቸጋሪ በመሆኑ ሁሉም የኮንደሚኒዬም ነዋሪ የወረዳው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በሚያዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ቆሻሻ በሚወጣበት ፕሮግራም መሰረት የቆሻሻው አመንጪ በተዘጋጀለት ቦታ ላይ ደረቅ ቆሻሻውን አውጥቶ እንዲያስቀምጥ በማድረግ በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት እንዲሰበሰብ መደረግ አለበት፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፭ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ቆሻሻ ከሚወጣበት ቀንና ሰዓት ፕሮግራም ውጪ ማንኛውም የኮንደሚኒየም ነዋሪ ቆሻሻ አውጥቶ መሬት ላይ ማስቀመጥ ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡

፯. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ለነዋሪው ህብረተሰብ አገልግሎት ሲሰጥ ኤጀንሲው ከዚህ በታች ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት በየቤቱ ቆሻሻ ሲያወጣ ደረቅ ቆሻሻውን ላስረከበው አባወራ ወይም እማወራ ቆሻሻውን ያወጣበትን ቀን በመጻፍ ምልክት ማድረግ ወይም ቀኑን የመጻፍ ግዴታ አለበት፡፡

፰. በዚህ አንቀጽ በቁጥር ፯ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የደረቅ ቆሻሻ ማውጫ መከታተያ ቅጽ በኤጀንሲው ወይንም በክፍለ ከተማው በየአመቱ እየታተመ ለነዋሪው በነጻ ወይም በክፍያ ይሰጣል፡፡

፰. በቅጹ ግርጌ ላይ የጥቆማ መስጫ ስልክ ቁጥሮች ማለትም የኤጀንሲው፣ የክፍለ ከተማውና የወረዳው እንዲጻፍ ይደረጋል፡፡

፱. የቅጹ ህትመት ሲከናወን የክፍለ ከተማውና የወረዳው ስም እንዲሁም ቅጹ የሚያገለግልበት ቀን ተጽፎ መታተም ይገባዋል፡፡

| በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ከመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ ለማውጣታቸው መከታተያ ቅጽ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅጹ የሚያገለግልበት ቀን …./……./…. ዓ.ም እስከ …./……./…… ዓ.ም | | | | | | |
| | | ክ/ከተማ…………………<br>ወረዳ …………………… | | | | |
| **ወራት** | **ሳምንት 1** | **ሳምንት 2** | **ሳምንት 3** | **ሳምንት 4** | **ሳምንት 5** | **ምርመራ** |
| **መስከረም** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ጥቅምት** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ህዳር** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ታህሳስ** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ጥር** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **የካቲት** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **መጋቢት** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ሚያዚያ** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ግንቦት** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ሰኔ** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ሀምሌ** | | | | | | |
| | | | | | | |
| **ነሀሴ** | | | | | | |
| | | | | | | |

## ፯. የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ ማከማቻ ግብዓት አቀራረብና ስታንዳርድ

፩. ማንኛውም የከተማው ነዋሪ ህብረተሰብ ለሚያመነጨው ደረቅ ቆሻሻ በራሱ ወጪ የቆሻሻ ፍሳሽን ማያንጠባጥብ የማዳበሪያ ቀረጢት፤ የፕላስቲክ ቀረጢት ወይንም ክዳን ያለው የፕላስቲክ የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫዎችን በራሱ ወጪ ገዝቶ በማህበራት እስከሚነሳለት ድረስ በግቢው ውስጥ የማጠራቀም ግዴታ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የፕላስቲክ ቀረጢት ለቆሻሻ ማጠራቀሚያነት የሚጠቀም ማንኛውም ነዋሪ የፕላስቲኩ መጠን ከ0.03 ሚሊ ሜትር ውፍረት በላይ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም የማዳበሪያውና የፕላስቲኩ ቀረጢት የመያዝ አቅሙ ከ50 ኪሎ ግራም መብለጥ የለበትም፡፡

፫. ከመኖሪያ ቤቶች ደረቅ ቆሻሻ የሚጠራቀምበት ግብዓት ቀለም ሁለት አይነት ሲሆን እነርሱም አረንጓዴ ለሚበሰብስ እንዲሁም ሰማያዊ ደግሞ ለማይበሰብስ መሆን ይገባዋል፡፡

፬. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በዓይነት ተለይቶ የተጠራቀመውን ደረቅ ቆሻሻ ቢያንስ በሳምንት ሁለት ቀናት የመሰብሰብ ግዴታ አለበት፡፡

፭. ማንኛው የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ከመኖሪያ ቤት ለሚቀበለው ደረቅ ቆሻሻ ተለዋጭ ማጠራቀሚያ ግብዓት የመስጠት ወይንም ማህበሩ በራሱ እቃ ገልብጦ የግለሰቡን ማስቀመጫ እቃ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

፮. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እቃዎችን በራሱ ወጪ ገዝቶ ወይንም ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት በተመጣጣኝ ዋጋ ቤት ለቤት ለነዋሪው ህብረተሰብ በማቅረብና በመሸጥ ተጨማሪ ገቢ ማግኘት ይችላል፡፡ ነገር ግን ነዋሪው ህብረተሰብ ከማህበራት ብቻ ማጠራቀሚያውን እንዲገዛ አይገደድም፡፡

## ፰. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የክፍያ ስርዓት

፩. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ክፍያ በሰበሰቡት የደረቅ ቆሻሻ መጠን ልክ በየወሩ በክፍለ ከተማው ተረጋግጦ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

፪. ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ደረቅ ቆሻሻ ለሚሰበስቡበት ክፍያ ተመን የሚወሰነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ካቢኔ ከወሰነው ክፍያ ውስጥ 85 ፐርሰንቱ ማህበሩ ደረቅ ቆሻሻ ለሰበሰበበት የሚከፈል ሲሆን ቀሪው 15 ፐርሰንቱ ክፍያ ደግሞ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ አገልግሎት የሚሰጥበት የዞን ጽዳትና ማህበሩ በስታንዳርዱ መሰረት ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠቱ በየወሩ ተረጋግጦ የሚከፈል ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፫ በተገለፀው መሰረት 85 ፐርሰንቱ ክፍያ ከማስወገጃ ቦታ የሚመጣ ደረሰን ማስረጃ ተደርጎ የሚከፈል ሲሆን ቀሪው 15 ፐርሰንቱ ማበረታቻ ክፍያ ደግሞ የወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ የህብረት ሽርክና ማህበሩ አገልግሎት የሚሰጥበትን ዞን ሙሉ በሙሉ ጽዱ ነው እንዲሁም ሁሉም የወረዳው ነዋሪ ህብረተሰብ በስታንዳርዱ መሰረት በሳምንት ሁለቴ ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ያገኘ ስለሆነ ለሽርክና ማህበሩ 15 ፐርሰንቱ ይከፈለው የሚል ህጋዊ ደብዳቤ ሪፖርት በየወሩ ለክፍለ ከተማው ሲጽፍ ብቻ ሆኖ ነገር ግን ክፍለ ከተማው በየወረዳው በመስክ ወርዶ የማጣራት ግዴታ አለበት፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፬ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ዞኑ ጽዱ አይደለም ወይንም በስታንዳርዱ መሰረት ነዋሪው ህብረተሰብ አገልግሎት አላገኘም ብሎ ደብዳቤ ከጻፈና ክፍለ ከተማውም ወርዶ ካረጋገጠ ችግር ባለበት ዞን አካባቢ የሚሰሩ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት 15 ፐርሰንቱ የወሩ ክፍያ ዋጋ ተቀናሽ ሆኖ ሌላው ደረቅ ቆሻሻ የሰበሰቡበት ገንዘብ ግን እንዲከፈላቸው ይደረጋል፡፡

፮. ማንኛውም ክፍለ ከተማ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራትን ወርሃዊ ክፍያ ሲሰራ ከማስወገጃ ቦታ የመጣውን መረጃና ከወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት የሚላክን የዞን ጽዳትና በስታንዳርድ መሰረት የጽዳት ማህበሩ አገልግሎት ለመሰጠቱ የተጻፈ ህጋዊ ደብዳቤ እና ክፍለ ከተማው በመስክ ወርዶ ያረጋገጠበትን ሪፖርት በማመሳከር መሆን ይገባዋል፡፡ ይህንን ሳያደርግ ክፍያ

የፈፀመ ማንኛውም አካል የመንግስት ንብረትን አላግባብ እንዳባከነ ተቆጥሮ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፯. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ክፍያ የወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ አገናዝቦ የከተማው አስተዳደር ካቢኔ በሚወስነው መሰረት የሚሻሻል ይሆናል፡፡ ስለዚህ ማንኛውም የህበረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በየአመቱ ከክፍለ ከተማ ጋር ውል ሲዋዋል በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ዋጋው ላይ ተስማምቶና ፈርሞ ስራ መጀመር ይገባዋል፡፡ ውል የተዋዋለ ማንኛውም የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበር በውሉ መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፰. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ወርሃዊ ክፍያ አስፈላጊው ማጣራት በክፍለ ከተማው ተደርጎ ከቀን 25-27 ድረስ በየወሩ ለማህበራት ክፍያ መፈፀም ይገባዋል፡፡

## ፱. የስራ ውል ስለመዋዋል

፩. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻን ከመኖሪያ ቤት ለመሰብሰብ በክፍለ ከተማ ደረጃ በየአመቱ የስራ ውል መፈራረም ግዴታ አለበት፡፡ በዚህም መሰረት በየዓመቱ ማንኛውም ክፍለ ከተማ ከሀምሌ 1 — 15 ባሉት ቀናት ውስጥ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ በክፍለ ከተማ ቀርቦ እንዲዋዋሉ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ ውሉ ላልታደሰ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ክፍያ አይፈፀምለትም፡፡

፪. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ ከክፍለ ከተማው ጋር የሚዋዋሉት ውል ፎርማት በኤጀንሲ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ክፍለ ከተማ የሚላክ ሲሆን ሁለቱ ተዋዋይ አካላት የተዋዋሉትን ውል በአራት ኮፒ በመፈራረም አንድ ኮፒ ለኤጀንሲው፤ አንደኛውን ኮፒ ለክፍለ ከተማ፤ አንደኛውን ኮፒ ደግሞ ለወረዳው ቀሪውን ደግሞ ለህብረት ሽርክና ማህበሩ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

፫. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በየዓመቱ ውሉን ከክፍለ ከተማ ጋር ሲያሳድስ ከወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይጠበቅበታል

1. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ የዞን ጽዳት በአግባበቡ እያፀዳ የነበረ ለመሆኑን፤
2. የህብረት ሽርክና ማህበሩ ለነዋሪው ህብረተሰብ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ለመሆኑ፤
3. ማህበሩ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ተጠቅሞ ስራዎች ሲሰራ የነበረ ለመሆኑ፤
4. ከየሽርክና ማህበሩ ከነዋሪው ህብረተሰብ ተጨማሪ ክፍያ አለመጠየቁ
5. የማህበሩ አባላት መልካም ስነምግባር ያላቸው ለመሆኑ የሚገልጽ ደብዳቤ ከወረዳው አጽፎ ለክፍለ ከተማው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በማቅረብ መዋዋል ይችላል፡፡

፬. ማንናውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፫ ከ1-5 ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱን ወይንም ከአንድ በላይ ካላሟላ ክፍለ ከተማው በደብዳቤ ለማህበሩ ችግሩን ጠቅሶ ለቀጣይ ዓመት ውል ሲያሳድስ እንዲያሻሽል የጽሁፍ በማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲመዘገብ መደረግ ይገባዋል፡፡

፭. በማስጠንቀቂያ የተመዘገበ ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በአመቱ ማስጠንቀቂያ የተሰጠውን ተግባር አሻሽሎ ካልቀረበ ውሉ አይታደስለትም፡፡

፮. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር የስራ ውሉን ከክፍለ ከተማው ጋር ሲያድስ በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፫ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሁሉም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ አባላት የቴታነስ ክትባት የተከተቡበት ማስረጃ ማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

፯. በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ የተሰማራ ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ከአምስት ዓመት በኋላ እራሱን አሳድጎ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ በመቀየር የደረቅ ቆሻሻ ማሰባሰብ ስራውን ለሌሎቹ መልቀቅ ግዴታ አለበት፡፡

፰. በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ የተሰማራ ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ከአምስት ዓመት በኋላ እራሱን አሳድጎ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ የመቀየር ግዴታ ያለበት በመሆኑ ማንኛውም ክፍለ ከተማ ከአምስት አመት በላይ ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ የተሰማራን የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበርን ውል ማደስ የተከለከለ ነው፡፡ በምትኩም ቅድመ ዝግጅት በማድረግ አዲስ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ተደራጅቶ እንዲገባ ማድረግ ይገባል፡፡

፱. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፰ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ረጅም ዓመታት ያስቆጠሩ ቢሆኑም አሁን ላይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ሌላ ዘርፍ ማሳደግ አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት አመታት ውስጥ ራሳቸውን አዘጋጅተውና ተገቢውን ቁጠባ አስቀምጠው ወደ ሌላ ዘርፍ መሸጋገር ግዴታ አለባቸው፡፡

## ፲. የደህንነት መጠበቂያና ግብዓት ስለማሟላት

፩. ማንኛው የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብና ሲያጓጉዝ የደህንንት መጠበቂያ ግብዓት (ማስክ፤ ሴፍቲ ጫማ፤ ሄልሜትና ቀይ አንፀባራቂ ልብስ) ማድረግ ይገባዋል፡፡

፪. የማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብና ሲያጓጉዝ ብርቱካናማ ቱታና ባጅ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

፫. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ ሰራተኞች ቱታ ሁሌም ንፁህ መሆን ይገባል፡፡ ንጹህ ያልሆነ የስራ ልብስ ለብሶ ከመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ የተከለከለ ነው፡፡

፬. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የደህንነት መጠበቂያና ቱታ ግዥ የሚከናዎነው ከማህበሩ አባላት በየወሩ ገንዘብ እንዲቆረጥ ተደርጎ ለማህበራቱ አባላት በሙሉ በጋራ በ6 ወር ወይም በዓመት ግብዓቱ እንዲገዛላቸው መደረግ አለበት፡፡

፭. ይህ መመሪ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ አሁን በስራ ላይ የሚገን ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት ቢያንስ ሰማያዊ ቱታውን ገዝቶ በመልበስ አገልግሎት መስጠት ግዴታ አለበት፡፡ እንዲሁም ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከስድት ወር በኋላ ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን የደህንነት መጠበቂያ ግብዓቶችን ገዝቶ የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፩. አዲስ የህብረት ሽርክና ማህበራት ስለማደራጀት

፩. ክፍለ ከተማው ማስፋፊያ አካባቢ ከሆነና በአካባቢው ከመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ የንብረት ሽርክና ጽዳትበ ማህበራት ከሌሉ ክፍለ ከተማው ኤጀንሲውን በደብዳቤ ጠይቆ ኤጀንሲው በአካባቢው ማህበራት መደራጀት እንዳለበት በባለሙያ

በመስክ ወርዶ ሲያረጋግጥ ብቻ አዲስ የሸርክና ማህበር አደራጅተው ወደ ስራ ማስገባት ይችላሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ነባር የሸርክና ማህበራት ሥራው ከመስፋቱ የተነሳ ከአቅም በላይ ሲሆንባቸው ወይም የማህበሩ አባላት ስራቸውን በተለያዩ ምክንያት ካቋረጡ ክፍለ ከተማውና ወረዳው ተነጋግረው የማህበሩን አባላት እንዲያሟሉ ያደርጋል፡፡

፫. የህብረት ሸርክና የጽዳት ማህበራት በአምስት አመታቸው ተመርቀው ወደ ሌላ ካደጉ ክፍለ ከተማውና ወረዳው በመነጋገር በምትካቸው አዲስ የህብረት ሸርክና ጽዳት ማህበር ተደራጅቶ እንዲገባ ማድረግ ይችላሉ፡፡

## ፲፪. የስራ አገልግሎትን ውል ስለመሰረዝ

፩. ማንኛውም የህብረት ሸርክና የጽዳት ማህበር ከነዋሪው ህብረተሰብ ተጨማሪ ክፍያ ከተቀበለ፣ ከወረዳው ፈቃድ ውጪ ከተቋማትና ከተለያዩ ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብ ከተገኘ የወረዳው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ለሶስት የተለያዩ ጊዜያት በደብዳቤ ችግሩን እንዲያስተካክል ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ማስጠንቀቂያ የማይታረም ከሆነ የህብረት ሸርክና ጽዳት ማህበሩ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ እንዲሰረዝ ተደርጎ በምትኩ አዲስ ማህበር እንዲደራጅና እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

፪. ማንኛውም የህብረት ሸርክና የጽዳት ማህበር የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት በአድማ በመሳተፍ ደረቅ ቆሻሻ መሰብበስ ካቆመ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ ተቋርጦ በምትኩ አዲስ የህብረት ሸርክና የጽዳት ማህበር ተደራጅቶ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ውሉ ሲቋረጥ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስርዓቱ ላይ ክፍተት እንዳይፈጠር የወረዳውና የክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊዎች በመነጋገር በሌላ ዞን ላይ የሚሰበስቡ ማህበራትን በማነጋገር ለጊዜው ሥራውን እንዲሸፍኑ መደረግ ይገባዋል፡፡

፫. ማንኛውም የህብረት ሸርክና የጽዳት ማህበር የዞን ጽዳት ሙሉ በሙሉ ባለማጽዳት እንዲሁም በስታንዳርዱ መሰረት ለነዋሪው ህብረተሰብ በሳምንት ሁለት ጊዜ የደረቅ

ቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት ባለመፈፀሙ ለአምስት የተለያዩ ጊዜያት 15 ፐርሰንቱ ከተቀጣ ወይም ካልተከፈለውና ለስድስተኛ ጊዜ የህበረት ሽርክና ጽዳት ማህበሩ ስህተት ፈጽሞ 15 ፐርሰንቱ ከተቀጣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ ይቋረጣል፡፡

## ፲፫. ቅጣትን በተመለከተ

፩. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስብበት የዞን ጽዳት ሙሉ በሙሉ ካላፀዳ እንዲሁም በስታንዳርዱ መሰረት ለነዋሪው ህብረተሰብ በሳምንት ሁለት ቀን ደረቅ ቆሻሻ ካላወጣ 15 ፐርሰንቱ ማበረታቻ አይከፈለውም፡፡

፪. ማንኛውም የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት የዞን ጽዳትና ነዋሪው ህብረተሰብ በሳምንት ሁለቴ አገልግሎት ማግኘቱን ሳያረጋግጥ ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ 15 ፐርሰንቱ እንዲከፈለው በሰጠው ማረጋገጫ ደብዳቤ ሪፖርት ምክንያት ማህበሩ ያልሰራበትን ክፍያ እንዲከፈለው ከተደረገ ይህንን ሳያረጋግጥ የሀሰት ሪፖርት ያቀረበው የክፍል ከተማውም ይሁን የወረዳው የክትትልና ድጋፍ ቡድን አባል በዲሲፕሊን እንዲጠየቅ በማድረግ ይህንን የሀሰት ሪፖርት በመስክ አረጋግጫለሁ ብሎ ያቀረበው ግለሰብ የባከነውን የመንግስት ገንዘብ እንዲመልስ መደረግ ይገባዋል፡፡

## ፲፬. የመረጃ አያያዝና ሪፖርት

፩. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከወረዳው ጽ/ቤት ጋር በመሆን አገልግሎት የሚሰጠውን አባወራና እማወራ በስም፣ በቤት ቁጥርና በቀጠና መዝግቦ የተደራጀ መረጃ መያዝ ይገባቸዋል፡፡

፪. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት አገልግሎት የሚሰጡትን አባወራና እማወራ ቋሚ ፕሮግራም በግልጽ መዝግቦ በሰነድ ማስቀመጥ ይገባዋል፡፡

፫. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና መጫን ስራ ጋር በተያያዘ በየወሩ ያከናወነውን ስራ፣ በዝርዝር እንዲሁም ያጋጠማቸውን ችግሮችና የተፈቱበትን አግባብ የሚያሳይ የጽሁፍ ሪፖርት ለወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በየወሩ የማቅረብና የመገምገም ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና መጫን ስራ ጋር በተያያዘ በየሩብ አመቱ ያከናወነውን ስራ፤ በዝርዝር እንዲሁም ያጋጠማቸውን ችግሮችና የተፈቱበትን አግባብ የሚያሳይ የጽሁፍ ሪፖርት ለክፍለ ከተማው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት የማቅረብና የመገምገም ግዴታ አለበት፡፡

፭. የእያንዳንዱ የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት ፋይል ለየብቻ በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ አደራጅቶ በማስቀመጥ የህብረት ሽርክና ማህበሩ የሚገልጹ ማንኛውም ማስረጃ ኮፒ ተጠርዞ ሊቀመጥ ይገባዋል፡፡

## ፲፰. የስራ ቦታ አድራሻ

፩. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ተከራይቶ ወይም በጊዚያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ቦታው አካባቢ ቋሚ ቢሮ ሊኖረው ይገባል፡፤

፪. በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ ቢሮው ጽዱና ውስጡም ባለጉዳይ የሚያርፍበት ወንበርና የጽፈት መሳሪያዎች ማሟላት ግዴታ ነው፡፡

፫. በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ ቢሮው ላይ የማህበሩ እና የአመራር አካላት ስም መለጠፍ ይገባዋል

## ፲፱. ከቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ተሽከርካሪ አይነት

፩. የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት ደረቅ ቆሻሻ ከቤት ለቤት የሚሰበስቡበት ተሽከርካሪ ለማውረድና ለመጫን የሚወስደውን ድካምና ጊዜ ለመቀነስ እንዲቻል ከዚህ በኋላ ማህበራት የሚገዙት ተሽከርካሪ ገልባጭ መሆን ይገባዋል፡፡

፪. የሽርክና ማህበራት ተሽከርካሪ ቀላልና የመጫን አቅሙ ከ30 ኩንታል መብለጥ የለበትም

፫. ማንኛው የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በተሽከርካሪው ጎን የሽርክና ማህበሩን ስም እና አዳራሽ የሚገልጽ ጽሁፍ መጻፍ ወይም በስቲከር መለጠፍ ይገባዋል፡፡

## ፲፯. የዞን ጽዳት ስለማከናዎን

፩. ማንኛው የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በየሳምንቱ ቅዳሜ ጠዋት የዞን ጽዳት ቀን ሆኖ ሁሉንም አባላቱን ያሳተፈ የጽዳት ስራ የሳምንቱ የማከናዎን ግዴታ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር የዞን ጽዳት ለመጠበቅ የሰው ኃይል እጥረትና የአቅም ውስንነት ካለበት በ15 ፐርሰንቱ የማበረታቻ ክፍያ የዞን ጽዳት የሚያፀዱ ሰራተኞችን በማህበሩ ወጪ ቀጥሮ ማጸዳትና ክፍያውን ከማህበሩ ተቀናሽ አድርጎ መክፈል ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህንን ለመፈፀም የህብረት ሽርክና ጽደት ማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት መስማማት ይገባቸዋል፡፡

፫. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በወሩ መጨረሻ በሚደረገው የህዝብ ንቅናቄ ጽዳት ላይ አገልግሎት ከሚሰጠው ዞን ከሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር በመሆን በጽዳት ስራው የመቀስቀስና የመሳተፍ  ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፰. የቅሬታ አፈታት

፩. ማንኛውም የወረዳ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት አገልግሎት በሚሰጡበት ወረዳ የሚያነሱትን ቅሬታ የሚፈታ ሶስት አባላት ያሉት ***"የማህበራት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ"*** በሚል ስያሜ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቋቋም ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር 15 ፐርሰንቱ ማበረታቻ ክፍያ በዞን ጽዳት ወይንም ለህብረተሰቡ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ባለመስጠቱ ቢቆረጥበትና የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበሩ የተቆረጠው ገንዘብ ተገቢነት የለውም ብሎ ካመነ ቅጣቱን ላስተላለፈው ወረዳ የማህበራት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በማስረጃ በማቅረብ ቅጣቱ እንዲነሳለት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ የማህበራት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የህብረት ሽርክና ማህበሩ ያቀረበውን ቅሬታ በማጣራት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይገባዋል፡፡

፬. በወረዳው የማህበራት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅጣቱ ተጣርቶ እንዲነሳለት የተወሰነለት ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር የቅሬታ ሰሚውን ኮሚቴ የውሳኔ ቃለጉባኤ በማካተት የወረዳው የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ህጋዊ ደብዳቤ ለክፍለ ከተማው ልኮ የተቆረጠው ክፍያ ለማህበሩ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

፭. ማንኛውም አካል በተደጋጋሚ ለሁለት ጊዜ በተሳሳተ ማስረጃ ወይንም በተለያዩ ምክንያቶች የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራትን 15 ፐርሰንት ማበረታቻ ክፍያ እንዲቀነስ ያስደረገ ግለሰብ በዲሲፐሊን ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡

## ፲፱. የክትትልና ድጋፍ አግባብ

፩. ማንኛውም የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት የወረዳ የዞን ጽዳትና የስታንዳርድ አተገባበርን የሚከታተል ሶስት አባላት ያሉት የክትትልና ድጋፍ ቡድን ማቋቋም አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፩ በተገለፀው መሰረት የክትትልና ድጋፍ ቡድኑ በየሳምንቱ በመስክ በመውረድ የዞን ጽዳትን እና ነዋሪው ህብረተሰብ በሳምንት ሁለቴ አገልግሎት እያገኘ መሆኑን ይከታተላል ውጤቱንም ከወረዳው ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር በመሆን በቃለ ጉባኤ በመመዝገብ በየሳምንቱ ይገመግማል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ በተገለፀው መሰረት ማንኛውም የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በክትትልና ድጋፍ ኮሚቴው በየሳምንቱ የተገመገመውን የመስክ ምልከታ ውጤት መነሻ በማድረግ ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት 15 ፐርሰንቱ ማበረታቻ ክፍያ እንዲከፈል የዞን ጽዳትና ህብረተሰቡ በስታንዳርዱ መሰረት በሳምንት ሁለቴ አገልግሎት ማግኘቱን የሚያረጋግጥ ሪፖርት በህጋዊ የደብዳቤ በየወሩ እስከ ቀን 20 ድረስ ለክፍለ ከተማው የማድረስ ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም ክፍለ ከተማ በወረዳ የተከናዎነውን የዞን ጽዳትና የስታንዳርድ አተገባበርን በመስክ ወርዶ የሚከታተል ሶስት አባላት ያሉት የክትትልና ድጋፍ ቡድን ማቋቋም ይገባዋል፡፡

፭. ማንኛውም ክፍለ ከተማ በወረዳ የተከናዎነውን የዞን ጽዳትና የስታንዳርድ አተገባበርን በመስክ ወርዶ የሚከታተለው የክትትልና ድጋፍ ቡድን በየሳምንቱ

የሚያቀርበውን ሪፖርት የክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ ጽ/ቤት ኃላፊ በተገኙበት በየሳምንቱ በቃል ጉባኤ የመገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡

፮. ማንኛውም ክፍለ ከተማ ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት 15 ፐርሰንት የማበረታቻ ክፍያ መክፈል የሚችለው ከወረዳዎች የሚመጣውን የዞን ጽዳትና ህብረተሰቡ በስታንዳርዱ መሰረት በሳምንት ሁለቴ አገልግሎት ማግኘቱን የሚገልጸውን የወረዳው ሪፖርት መነሻ በማድረግና የክፍለ ከተማው የክትትልና ድጋፍ ቡድን በመስክ ወርዶ በማረጋገጥ በሚያቀርበው የተገመገመ ሪፖርት መሰረት በማድረግ ብቻ ነው፡፡

፯. የዞን ፅዳት እና የስታንዳርድ አፈፃፀሞች በሚጠበቀው ደረጃ እየተፈፀመ ክፍያ የሚከፈል ስለመሆኑ ኤጀንሲው ራሱን የቻለ የክትትልና ቁጥጥር ቡድንና ስርዓት በመዘርጋት ማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

# <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

### ፳. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት

፩. የህብረት ሽርክና ማህበራት የሚሰሩበትን የአሰራር ስታንዳርድ ያዘጋጃል፡፡

፪. በከተማው የሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራትን ከክፍለ ከተማው ጽ/ቤት ጋር በመሆን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፫. ለህብረት ሽርክና ማህበራት ከክፍለ ከተማው ጋር በመቀናጀት የአቅም ግንባታና የክህሎት ስልጠና ይሰጣል፡፡

፬. ወቅታዊ የማህበራትን ክፍያ ጥናት በማስጠናት ከከተማው ስራ አስኪያጅ ጋር በመሆን በካቢኔ እንዲፀድቅ ያደርጋል፡፡

### ፳፩. የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

፩. በክፍለ ከተማው ውስጥ የሚገኙትን የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ውል በየአመቱ ያድሳል፡፡

፪. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የማበረታቻ 15% ክፍያ ለመፈፀም የዞን ፅዳት እና ለህብረተሰቡ የተሰጡ የአገልግሎት ስታንዳርዶች አፈጻጸም ከወረዳ በመጣው ሪፖርት መነሻነትና በመስክ ወረዶ በማረጋገጠ ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

፫. በክፍለ ከተማው ለሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት በክፍለ ከተማው በሚገኙ የግንዛቤ ባለሙያዎች አማካኝነት በቋሚነት የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡

፬. በአገልግሎት አሰጣጡ ከተገልጋዩ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለይቶ ወቅታዊና አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል፡፡

፭. በቋሚነት በየሩብ ዓመቱ የሽርክና ማህበሩን ሪፖርት መነሻ በማድረግ ስራዎችን ይገመግማል፡፡ አስፈላጊውን ማስተካከያም በመመሪያው መሰረት ያደርጋል፡፡

፮. በክፍለ ከተማው የሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት በዚህ መመሪያ መሰረት ስራቸውን እንዲሰሩ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ በመመሪያው መሰረት ይወስዳል፡፡

## ፳፪. የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

፩. በወረዳው የሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት አገልግሎት የሚሰጡባቸውን አባወራና እማወራ በቤት ቁጥርና በቀጠና መዝግቦ ያደራጃል፡፡

፪. በወረዳው በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት አገልግሎት የሚያገኙ አባወራና እማወራ የአገልግሎት ቀኑ መቼ እንደሆነ መዝግቦ በሰነድ ያስቀምጣል፡፡

፫. በወረዳው የሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከመኖሪያ ቤት ውጭ (ከተለያዩ ተቋማት፤ የንግድ ድርጅቶች) ደረቅ ቆሻሻ እንዳያነሱ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ይከታተላል፤ ቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን ማስተካካያ ይወስዳል፡፤

፬. በወረዳው የሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ሪፖርትን መነሻ በማድረግ ስራዎችን በየወሩ ይገመግማል፡፡

፭. በወረዳው ለሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት በወረዳው በሚገኙ የግንዛቤ ባለሙያዎች አማካኝነት ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

፯. ለህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት የአባወራ መጠንን መሰረት ያደረገ ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡበትን ዞን ከልሎ በካርታ ለማህበራት ይሰጣል፡፡ በካርታው መሰረት አገልግሎት መሰጠቱን ባለሙያ መድቦ ይከታተላል፡፡ ካርታውንም በወረዳው ለጥፎ ያስቀምጣል፡፡

፰. ሁሉም የሽርክና ማህበራት የተመደቡበትን ዞን ንፅህና እና ሌሎች ተግባራትን በስታንዳርድ እንዲፈፅሙ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ሳይፈጽሙ የተገኙትን ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

፱. የህብረት ሽርክና ጽዳት ማህበራት የሚያቀርቡትን ቅሬታ የሚፈታ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽ/ቤቱ ያቋቁማል፡፡

፲. የዞን ጽዳትንና ነዋሪው አገልግሎቱን በስታንዳርዱ መሰረት እየሰጠ መሆኑን ከክትትልና ድጋፍ ባለሙያዎች ጋር በየሳምንቱ ይገመግማል፡፡

## ፳፫. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ተግባርና ግዴታ

፩. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት

፪. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር አገልግሎት በሚሰጥበት አካባቢ የሚገኘውን ዞን ጽዳት የማጽዳትና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በወርሃዊ የከተማ ጽዳት ላይ አገልግሎት በሚሰጥበት ወረዳ ላይ በመገኘት የመሳተፍ ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ከክፍለ ከተማው ጋር የተዋዋለውን ውል ለማቋረጥ ሲፈልግ ከማቋረጡ ከሁለት ወር በፊት ለክፍለ ከተማው በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፭. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በውሉ ተመላክቶ በተሰጠው የስራ ቦታ ብቻ አገልግሎቱን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፮. ኤጀንሲው ከሚከፍላቸው ክፍያ ውጪ ከነዋሪው ህብረተሰብ ተጨማሪ የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል የተከለከለ ነው፡፡

፯. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር በወሩ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ያዋለውን የደረቅ ቆሻሻ መጠንና ብር በየወሩ ለወረዳው (ለክፍለ ከተማው) ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፰. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ሁሉም አባላቱና ሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ማሟላትና ንጽህናቸውን እንዲጠበቁ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፱. ማንኛውም የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ደረቅ ቆሻሻ የሚያሰበስቡበትን ዕለት ለነዋሪዎች በግልጽ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፲. ደንበኞቻቸውን በማራኪ አቀራረብና ሰነ-ምግባር መያዝ፤ ስራቸውን በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ፣ በካይዘን ሥራ አመራር እንዲመራ ማድረግ አለባቸው፣

፲፩. ነዋሪው የሚያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ የሚበሰብስ እና የማይበሰብሰውን ለይቶ እንዲይዝ ከወረዳ የጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት የትምህርትና ቅስቀሳ ስራ መስራት፤

፲፪. በወርሃዊ ቋሚ የህዝብ ተሳትፎ ጽዳት ስራ አማካኝነት የተሰበሰበ ደረቅ ቆሻሻ በወቅቱ በመሰብሰብ ወደ ጊዚያዊ ማቆያ ጣቢያ ማጓጓዝ፤

፲፫. በተመደቡበት ዞን ህገ-ወጥ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ማፅዳት እና እንዳይቆሽሹ መጠበቅ አጥፊዎች ሲኖሩም ተከታትሎ እንዲከሰሱ መረጃ መስጠት

፲፬. ተገቢ ባልሆነ ቦታ ደረቅ ቆሻሻ የሚያሰወግዱ አካላትን መከታተል፣ መቆጣጠር እና ቆሻሻን በተገቢው እንዲይዙ ማስተማር፤ ለውጥ በማያመጡት ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤

፲፭. ጊዚያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ (ቅብብሎሽ ጣቢያ) በንፅህና እንዲጠበቅ፣ አረንጓዴ እንዲሆን ማድረግ፤ የተጠራቀመ ቆሻሻ በተገቢው እንዲጓጓዝ ማድረግ፤

፲፮. አባሎቻቸው ከሚያገኙት ገቢ ቢያንስ 20 በመቶ በመቆጠብ የዘመናዊ ደረቅ ቆሻሻ ተሸከርካሪ እና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለመሆን መንቀሳቀስና ከአምስት አመት በኋላ ወደ ሌላ ዘርፍ ለሚያደርጉት ዝውውር ዝግጅት ማድረግ፡፡

፲፯. የተመደቡበት ዞን መንገዶች፣ ቦዮች፣ የወንዝ ዳርቻና ወንዞች ከደረቅ ቆሻሻ የፀዳ እንዲሆን በኃላፊነት መስራት፤

፲፰. በሚቀመጠው መደበኛ የግንኙነትና የግምገማ አሰራር መሰረት ራሳቸውን እየፈተሹ ማስተካከል፣ አጥፊዎችን መቅጣት፣

፲፱. የሌብነትና የብልሹ አሰራር ሁኔታን መፀየፍና መከታተል፣ ንብረትን በስርአትና በግባቡ መያዝና መጠቀም፡፡

## ፳፬. ቆሻሻ የሚያመነጭ ነዋሪ ህብረተሰብ ተግባርና ኃላፊነት

፩. ማንኛውም መኖሪያ ቤት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በዓይነት በመለየት በፕሮግራሙ መሰረት ለህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም መኖሪያ ቤት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ አካባቢን ሳይበክል ኤጀንሲው በሚያወጣው የማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሰረት የማጠራቀምና የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

፫. የቤት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን ባልተገባ ቦታ አለመጣል፡፡

፬. የህብረት ሽርክና የፅዳት ማህበራቱን የአገልግሎት አሰጣጥ ሥራ መቆጣጠርና መከታተል፣ በህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበሩ ችግሮች ካሉ ማጋለጥ፣

፭. ከመኖሪያ ቤቱ እስከ 20 ሜትር ራዲዬስ ያሉ አጥር ጥግ ቦታዎችን፤ ክፍት ቦታዎችን፤ መንገዶችን፣ ውሀ መውረጃ ቦይ፣ ክፍት ዲሽ፣ ወዘተ ጽዱ፣ ውብ፣ አረንጓዴና ማራኪ ማድረግ፤

፮. በየወሩ በቋሚነት በሚካሄደው የጽዳት ተግባር ላይ እድሜው ከ18 እስከ 65 ዓመት የሚደርሱ የቤተሰብ አባላት በማሳተፍ አካባቢያቸውን ማፅዳት፤

፯. የደረቅ ቆሻሻ ባልተገባ ቦታ የሚያስወግዱትንና በየመንገዱ የሚፀዳዱትን አካላት ማስተማርና መምከር፤ ሳይታረሙ ሲቀሩ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ፤

፰. በጽዳትና አረንጓዴ ልማት የተሻለ ተሞክሮ ያላቸውን አካባቢዎች በአርአያነት በመውሰድ በራስ መንደር መተግበር፤

፱. በመንደራቸው ያለውን አደረጃጀት ማለትም እድር፣ የአካባቢ ልማት ኮሚቴ፣ ወዘተ ላይ የፅዳትና ውበት ተግባርን እንደ አንድ አጀንዳ በማድረግ ዘውትር መወያየት፤ መነጋገር፤

፲. በፅዳት ተግባር ዙሪያ የወረዳው አስተዳደር የሚያደርጋቸው ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ፤

፲፩. በየመንገዱ የሚቀመጡ አነስተኛ የቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎች (ደስት ቢን) በሃላፊነት መቆጣጠርና መንከባከብ፣ አጥፊዎች ሲኖሩ በቶሎ ለህግ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

**፳፩. የተጠያቂነት ስርዓት**

- ❖ ማንኛውም አካል በዚህ መመሪያ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ካልፈፀመ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፪. መመሪውያውን ስለማሻሻል**

- ❖ ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሊያሻሽል ይችላል

**፳፫. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

- ❖ ይህ መመሪያ ከዛሬ 01/08/2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

# በአዲስ አባባ ከተማ አስተዳዳር

# የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ